# ጄኔራል ፃድቃን፣ ኢሕአዴግና የሰሜን አፍሪካ አብዮት

**(ክፍል ሁለት)**

**እስክንድር ነጋ**

**አዲስ አበባ**

***መግቢያ***

«ሻይ፤ በሎሚ፣ ያለስኳር» አልኳት፤ ትዕዛዝ ልትቀበለኝ ፊት ለፊቴ የቆመችውን ወጣት::

ትላንት፤ ሰኞ፣ የካቲት 28 ቀን 2003 ዓ.ም፤ ከጠዋቱ 2 ሰዓት:: ኢንተርኔት ካፌ እስከሚከፈት ሚጢጢ ሻይ ቤት ውስጥ ቁጭ ብያለኹ:: በእጄ «OBAMA» የሚባለውን ቢጫ እስክሪቢቶ ይዣለኹ:: ጠረጴዛ ላይ ወረቀት አስፍሬያለኹ:: የጀኔራል ፃድቃንን ክፍል ሁለት መጣጥፍ ለመጀመር እያቅማማኹ ነው:: ቴሌቪዥኑ ትኩረቴን እየተሻማው ነው:: የኒክ ኒልቴ የድሮ ፊልም በዐረብ ሳት እየተላለፈ ነው:: ፊት ለፊቴ ሶስት ሰዎች ሞቅ ያለ ጨዋታ ይዘዋል:: አንዱ ሽበት ጣል ጣል አድርጎባቸዋል:: ሁለቱ ወጣቶች ናቸው::

«ዜና ላይ አድርጊው...» አለ ወጣቱ ወደ ባሬስታዋ ዞር ብሎ::

ባሬስታ ሆና የምትሰራው የሻይ ቤቷ ባለቤት ናት:: ከደንበኞቿ ጋር ትግባባለች::

«ለምን?...»

«ስለማንቼ ጨዋታ ይኖራል...»

አላመነታችም:: ሪሞቱን ብድግ አድርጋ ኢቲቪ ላይ አደረገችው:: «ዜና» የሚለው ምስል ብልጭ አለ:: ዓይኔን ቶሎ ከቴሌቭዥኑ ላይ ነቀልኹ:: አሁን ትኩረቴ ሳይሰረቅ መፃፍ ልጀምር ነው:: እስከ ግማሽ ቀን ሁሉን ነገር መጨረስ አለብኝ::

«ጋዳፊ ወረደ እንዴ?...» ብላ ባሬስታዋ ስትጠይቅ ቀና አልኹኝ::

ይቺን ወጣት በመጠኑ አውቃታለኹ:: ፖለቲካ ስታወራ ሰምቼ አላውቅም:: ገረመኝ:: ነግዳ ትልቅ ቦታ ለመድረስ እንደምታልም ከዚህ በፊት አጫውታኛለች:: ከዚህ ሌላ የትኩረቷ ማዕከሏ አንዲት ህፃን ሴት ልጇ ነች::

«የቱ?...» ብሎ መለሰላት ወጣቱ::

«እንዴት?»

እሷ ብቻ አይደለችም:: የወጣቱ ጥያቄ እኔንም ግራ አጋብቶኛል:: ስንት ጋዳፊዎች አሉ? በዓለም የሚታወቀው አንድ ጋዳፊ ነው:: ምን ተዓምር ይዞ መጣ ይሄ ወጣት? ሁለተኛ ጋዳፊ አለ እንዴ?

«የእኛ ነው? የእነሱ?....» ብሎ መለሰላት ወጣቱ::

አብረውት የተቀመጡት ሻይ ቤቷን በሳቅ አደበላለቋት:: እኔ እስኪገባኝ ትንሽ ሴኮንዶችም ቢሆኑ ፈጁብኝ::

የእኛ?... ኦ... ኦ... ኦ... ኦ.... አሁን ገባኝ!!! እኔም ሳቄን ለቀቅኹት... የተራዘመ ሳቅ... ከውስጥ ፈንቅሎ ነው ያሳቀኝ... በትይዩዬ ከተቀመጠው ወጣት ጋር ዓይን ለዓይን ተገጣጥመን ተሳሳቅን:: ወጣቱ ቀጠለ::

«የእኛን ከሆነ አለ!...»

ሳቃችን ቀጠለ፡፡ እነዚህ ሰዎች ማንነቴን አያውቁም፡፡ ቅንጣት ያህል ግን አልፈሩኝም፡፡

ትልቁ የኢህአዴግ መሣሪያ በሕዝብ ላይ ያጠለቀው የፍርሃት ማነቆ ነው፡፡ እየተገረሰሰ ይሆን?

አእምሮዬ ተፍታታ... እጄ ተፍታታ... አሁን ደስ ደስ እያለኝ መፃፍ እችላለሁ... ቀኑ በሚያምር መልኩ ተጀምሯል... ለካ ሰኞ ነው... ሳምንቱ ሙሉ ብሩህ መስሎ ታየኝ!!

## ክፍል ሁለት

«ፃድቃን፣ ፃድቃን የምትለው ሰራዊቱን ለመከፋፈል ነው...» ብለው ኮምሽነሩ ፅሑፌን ብድግ አደረጉ፡፡ በግራ እጃቸው ወደ ሁለተኛው ገፅ ገለፁ፡፡

«ምንድንነው እዚህ ጋር ያልኸው?... እታች (ያለው ተራ ወታደር) የእኛ ነው፤ አይተኩስም፤ ነው የምትለው አይደል?...» ብለው ቆም አሉ፡፡

ዓይናችን ገጠመ፡፡ ዝምታ፡፡

«እላይ (ያሉት አዛዦች) አርጅተዋል?...»

ወረቀቱን ጠረጴዛው ላይ ጣሉት፡፡ ወደፊት ተለጠጡ፡፡ አሁን ከመቼውም ጊዜ በላይ በስሜት ነው የሚናገሩት፡፡

«አንተስ? ቆመህ የምትቀር ይመስልሃል? እንደ ቋንጣ ደርቀህ የምትቀር ይመስልሃል? አንተ አታረጅም?...»

ኮምሽነሩ አሁን ትንሽ የተነፈሱ ይመስላሉ፡፡ ተሽከርካሪ ወንበራቸው ላይ ወደኋላ ተንጋለው ተቀመጡ፡፡ አተኩረው ይመለከቱኛል፡፡

«ፃድቃን፣ ፃድቃን የተባለው፣ አሁን ያለው (ጄኔራል ሳሞራ የኑስ) ምንም አይደለም ማለት ነው? ዝም ብሎ የተቀመጠ ዕቃ ነው ማለት ነው?...»

«የፅሑፉ ይዘት ሌላ ነው...» ብዬ ለመጀመሪያ ጊዜ ጣልቃ ለመግባት ሞከርኹኝ፡፡ አልፈቀዱልኝም፡፡

«ስማ! የምትመኘው የግብፅና የቱኒዚያ ረብሻ ቢነሳ የሚሆነውን ልንገርህ፡፡ በዚህኛው ዙር የደሃ ልጅ አይሞትም፡፡ አንተ ጋር ነው መጀመሪያ የምንመጣው፡፡ እኛ የቆረጥን ሰዎች ነን፡፡ ልናስርህ አይደለም፡፡ እርምጃ ይወሰድብሃል...» በረጅሙ ተነፈሱ «ትሰማለህ? እርምጃ ይወሰድብሃል!! አንተን ማሰር ሰልችቶናል፡፡ ትሰማለህ? ሰልችቶናል!..... የቆረጥን ሰዎች ነን...» ድምፃቸው ትንሿን ክፍል እያናወጠው ነው፡፡ ፀሐፊዋ ክፍል እየተሰማ ስለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለኝም፡፡ የኮምሽነሩ ጩኸት እያስደነገጠኝ ነው፡፡

«አያደርጉትም ብለህ እንዳትሳሳት፡፡ ቀስቃሾቹ ላይ እርምጃ እንወስዳለን፡፡ የመንግሥት ውሳኔ ነው፡፡ እንድታውቀው፤ እንድትጠነቀቅ!» ብለው ደመደሙ ኮሚሽነሩ፤ ድምፃቸውን በመጠኑ ዝቅ አድርገው፡፡

የኮምሽነሩ ምቹ የቆዳ ሶፋ እንደ ድንገት የቆረቆረኝ መሰለኝ፡፡ ከበባድ ቃላት!... ከመንግሥት ከፍተኛ ባለስልጣን ዝም ብለው የተወረወሩ ቃላት አይደሉም፡፡ ኮምሽነሩም ዝም ብለው ቃላት የሚወረውሩ ሰውም አይመስሉም፡፡ የነባር ታጋይ ገፅታ ነው ያላቸው፡፡ የድርጊት እንጂ የቃላት ሰው መስለው አልታዩኝም፡፡ ዛቻቸው የምር ነው፡፡

«ሕግና ስርዓት ተከትዬ ነው የምሰራው፡፡ ሕገ-መንግሥቱ ዋስትና ይሆናል የሚል እምነት አለኝ...» አልኹኝ፡፡ ሆኖም ግን፣ በኢትዮጵያ፣ ሕግ ማለት ባለሥልጣናት መሆናቸውን አውቃለኹ፡፡ የፈቀዳቸውን ማድረግ ይችላሉ፡፡

የኮምሽነሩ ረዳት መለሱልኝ:: ሲናገሩ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው:: የአለቃቸውን ፍቃድ አልጠየቁም::

«ሕግ... ሕግ ትላለህ:: ግን ቆም ብለህ የምትፅፋቸውና የምትሰጣቸው ቃለ-ምልልሶች እያሳደሩ ያሉትን እንደምታ አጢነኸል?» አሉኝ፤ በፍጥነት በተወረወሩ ቃላት::

«ተጠንቅቄ በሕግ ጥላ ስር ነው የምንቀሳቀሰው..» ብዬ ገና ስጀምር አቋረጡኝ፤ የኮምሽነሩ ረዳት::

«ውስጠ ወይራ ናቸው:: ሕግ የተከተሉ ይመስላሉ፤ ግን የአመፅ ጥሪዎች ናቸው:: ከትላንት በስቲያ ከአሜሪካ ድምፅ ጋር ያደረከው ቃለ-ምልልስ የአመፅ ጥሪ ነው:: ውስጠ ወይራ አለው:: የአመፅ ጥሪ ነው ያስተላለፍከው:: በእኛ በኩል፣ በቂ መረጃ በእጃችን ይዘናል፤ አስፈላጊ ከሆነ...» ብለው ኮምሽነሩ ጠረጴዛ ላይ ወደተቀመጡት ወረቀቶች አመላከቱ::

ወረቀቶቹ ተከምረዋል:: ጎናቸው ትልቁ ቢጫ ፖስታ ተጋድሟል:: ብዙ ክስ እንደተዘጋጀልኝ ከሰማኹ ሰነባብቻለኹ:: እሱ ግን አላሳሰበኝም:: ከኮምሽነሩ ዛቻ አንፃር ኢምንት መስሎ ታየኝ::

«ስማ!...» ብለው እረዳታቸውን ተቀበሉ ኮምሽነሩ:: «ስማ!... ይሄ ሕግን የተከተለ ነው?» ብለው ከጠረጴዛው ላይ ጋዜጣ ብድግ አደረጉ:: እስካኹን አላየኹትም::

«አዲስ ወሬ» ጋዜጣ ነው:: «ኢሕአዴግ አምስት ዓመቱን ምርጫ ሳያደርግ እጨርሳለኹ የሚል ከሆነ፣ ችግር ይፈጠራል የሚል ግምት አለኝ» እስክንድር ነጋ፤ ይላል አርዕስቱ በትልልቅ ፊደላት:: ማክሰኞ እለት የወጣ ቃለ-ምልልሴ ነው::

«አዎ!... የምንከተለው የፓርላማ ስርዓት ነው:: ፓርላማ በማንኛውም ሰዓት ሊፈርስ ይችላል...»

«በፍፁም:: ይሄ ሕገወጥ ነው:: እንዴት ነው ሕጋዊ ሊሆን የሚችለው? መንግሥት ይፍረስ እያልክ ነው እኮ:: ኢ-ሕገመንግሥታዊ ነው:: ሕገ-መንግሥቱ በኃይል ይናድ ነው የምትለው!» ብለው ጮኹብኝ ኮምሽነሩ::

«እስክንድር ስማ!... አብቅተናል:: የተጠራኸው ማስጠንቀቂያ ሊሰጥህ ነው! ትሰማለህ?» አሉኝ ኮምሽነሩ አሁንም እየጮኹ::

«ተጠንቀቅ!.... ተጠንቀቅ!...» አሉኝ ሁለት ጊዜ፤ ሌባ ጣታቸውን እያወዛወዙ::

«ጨርሻለሁ...» አሉ ኮምሽነሩ ጠረጴዛቸው ላይ ያሉትን ወረቀቶች እንደማሰባሰብ እያሉ::

ከተቀመጥኹበት ብድግ አልኹኝ::

«መሄድ እችላለሁ ማለት ነው?» ብዬ ጠየቅኹኝ::

«አዎ!»

«አመሰግናለኹ...» ብዬ አጠገቤ ያለውን በር ከፈትኹት:: ፖሊሱ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ ኮምሽነሩ ቢሮ በር ላይ ቆመ:: በእጁ በኪሴና በእጄ ላይ የተገኙትን ወረቀቶች ይዟል::

«ከግቢው አስወጥተህ ልቀቀው» አሉት ኮምሽነሩ::

«እነዚህ በእጁ ላይ የተገኙ ናቸው» ብሎ ወረቀቶቹን ሰጣቸው::

ከፖሊሱ ጀርባ ቆሜ እየተመለከትኹ ነው:: ኮምሽነሩ ወረቀቶቹን ተቀበሉት:: በሙሉ በእንግሊዝኛ የተፃፉ ናቸው:: አልፈው አልፈው ቃኟቸው:: ለረዳታቸው አቀበሏቸው::

«ሂዱ...» አሉ ኮምሽነሩ::

ወረቀቶቹ በሙሉ ተወረሱ ማለት ነው:: ፖሊሱ በሩን ዘግቶ ሌሎች እቃዎቼን መለሰልኝ:: ለመውጣት ስንዘጋጅ ኮምሽነሩ እንደ ድንገት በራቸውን ከፍተው ደረሱብን::

«እስክንድር...»

«አቤት!»

«ስልክ ቁጥርህ ስንት ነው?»

እረዳታቸው የተቀመጡበት ሆነው ቁጥሩን ለመፃፍ እስክሪብቶ በእጃቸው ይዘዋል::

ነገርኳቸው:: እረዳታቸው በእጃቸው በያዙት ወረቀቱ ላይ ፃፉት::

ኮምሽነሩ ወደ ቢሮአቸው ተመለሱ:: ፖሊሱ ፊት ፊት እየቀደመ ተከታትለን ወጣን:: (ከኮምሽነሩ ጋር የነበረኝ ቆይታ በአጭሩ የቀረበ ነው:: አብዛኛውን ትቼዋለሁ::)

«ወዴት ነው የምትሄደው?» አለኝ ፖሊሱ ሽጉጡን ከተቀበለ በኋላ::

«ወደ ፒያሳ ነው፤ ወደዚያው ናችሁ እንዴ?»

«አይደለንም:: ግማሽ መንገድ ድረስ አብረኸን ትሄዳለህ::»

አሁንም ተንሸራትቼ ሹፌሩ ጎን ተቀመጥኩ:: መገናኛ የያዘው ፖሊስ ጐኔ ተቀመጠ::

«ሰላም ነው አይደል?» አለኝ፤ ጋቢና ውስጥ ከገባን በኋላ::

«ቀንተኸኛል» አልኩት ፈገግ ብዬ::

«እንዴት?» አለ፤በአግራሞት እየተመለከተኝ::

«ወደ እስር ቤት የምሄድ መስሎኝ ነበር:: ይኸው ወደቤቴ ልሄድ ነው» ስለው ከት ብሎ ሳቀ:: ቆፍጣናው ሹፌርም ለመጀመሪያ ጊዜ ፈገግ አለ::

«ብሔራዊ ጋር እናወርደዋለን» አለ መገናኛ የያዘው ፖሊስ:: ሹፌሩ ላንድ ክሩዘሯን አስነስቶ ቀስ ብሎ ግቢውን ለቆ ወጣ:: ሜክሲኮ አደባባይን አልፈን ዋቢሸበሌ ደረስን::

«ተግባባችሁ?» ብሎ ጠየቀኝ መገናኛ የያዘው ፖሊስ ፈራ ተባ እያለ::

«ዋናው ቁምነገር፣ ስላልተግባባን አለመገዳደላችን ነው» ብዬ መለስኩለት::

አንገቱን ወደላይ ወደታች ነቀነቀ:: መልስ ግን አልሰጠኝም:: ሾፌሩን ዞር ብዬ ተመለከትኩት:: ትኩረቱ መንገዱ ላይ ነው:: መኪና የሚበዛበት መንገድ ነው::

«እንዳንገዳደል ብዙ ወጣቶች መስዋዕትነት ከፍለዋል» ብዬ ቀጠልኩ::

ወዲያው መልስ አልሰጠኝም::

«የአንድ ሀገር ልጆች ነን:: ሁላችንም ኢትዮጵያዊ ነን:: የፖለቲካ ልዩነት በሰላም ሊያልቅ ይችላል:: መገዳደል የለብንም» አለ መገናኛ የያዘው ፖሊስ ከትንሽ ሴኮንዶች ዝምታ በኋላ::

ከልቡ መናገሩ ገፅታው ላይ ይነበባል::

ብሔራዊ ጀርባ ደረስን:: ተሰነባብተን ወረድኩኝ:: ታክሲ ተሳፍሬ ወደ ፒያሳ ዘለቅኩ::

መሐሙድ ሙዚቃ ቤት ጋር ወረድኩ:: የፒያሳን ንፁህ አየር በረጅሙ ተነፈስኩት:: አቤት ደስ ማለቱ::

የፖሊሱ አባባል ደግሞ ልቤን ነክቶታል::

ተስፋ አለን!